## ምዕራፍ አንድ

### ፩. ለምን እናጠናዋለን?

- ኢየሱስን ለማወቅ (ዮሐ 5፥39)
- ሚዛናዊና ትርጉም ያለው ኑሮ ለመኖር (ማቴ 4፥4)
- የድል ኑሮ ለመኖር (ኢያሱ 1፥7-8)
- የእግዚአብሔርን ተዓምር እንድናይ (መዝ 119፥18)
- እንደ እግዚአብሔር ሰዎች የተዘጋጀን እንድንሆን (2ጢሞ 3፥17)
- የቤተ ክርስቲያን ሀብት ነው፤ ስለዚህም ልናጠናው ይገባናል።

### ፪. በምናጠናበት ጊዜ፥

- የራሳችን የቃሉ መገለጥ ይኑረን (Discover The Word of God)
- በክፍሉ ዝርዝር ሐሳቦች እንጀምር
- በማስተዋል ደጋግመን እናንብበው (አዕምሮ)
- በመንፈስ ቅዱስ አስተማሪነት እንደገፍ
- በእርስ በርሳችንም እንደገፍ (በቡድን በምናጠናበት ጊዜ)
- በፀሎት እንጀምር፤ በዚያው መንፈስ እንቀጥል

### ፫. መፅሐፍ ቅዱስን ለመረዳት፥

#### *1. የመፅሐፍ ቅዱስ አሰሳ፥ (Bible Survey)*

- ዝርዝር ነገሮችን ሳንመለከት ጠቅላላ ትዕይንቱን መመልከት ነው
- ፀሐፊው የሰጣቸውን ዋና ነገሮችን፥ (High-lights)
- አጀማመሩንና አደማደሙን
- ምዕራፎቹ የሚቀባበሉትን እውነት
- የመፅሐፉን አጠቃላይ ሃሳብ እናያለን

***ልምምድ***፥ ማር 1፥1-45

#### *2. የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት፥*

- ከዝርዝር ሃሳቦች ተነስቶ ዋናውን ሃሳብ ለማየት የሚሞከርበት መንገድ ነው

<u>ጥናት ማለት፥</u>

- “እውቀትን ለማግኘትና ለማቆየት፥ ስርዓት በያዘ መንገድና በዓላማ  አእምሮን በመንፈስ ቅዱስ ቅባት አስተማሪነት መጠቀም ነው።

*<u>ከዚህ ትርጉም ውስጥ አራት ዋና ነገሮችን እናያለን፥</u>*

- እውቀትን ለማግኘትና ለማቆየት (Discovering & Retaining)
- ስርዓት በያዘ መንገድ (Systematic/Study Method)
- በዓላማ (Objective/Goal)
- አእምሮን መጠቀም (Open-mind)
- ለመንፈስ ቅዱስ ቅባት አስተማሪነት ልብን መክፈት (The Illumination of  the Holy Spirit)

*<u>3.  የጥሞና ጊዜ፥ (Bible Meditation)</u>*

- ባልተቻኮለ ልብ በአንድ ጥቅስ ወይንም እሳቤ (Concept) ማሰላሰል/ማውጠንጠን ነው

<u>፬. የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናቶች ልዩ ልዩ ገፅታ፥</u>

*<u>1.  ርዕሳዊ የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት፥ (Topical Bible Study)</u>*

<u>ምሳሌ፥</u> ስለ ፅድቅ፥ ቅድስና፥ ፀጋ፤ መንፈስ ቅዱስን ማጥናት።

<u>2.  የባህሪይ የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት፥ (Biographical/Character Bible Study)</u>

<u>ምሳሌ፥</u> ስለ ሙሴ፥ ዳዊት፥ ነህምያ፥ ዘሩባቤል፥ ጴጥሮስ፥ ዮሐንስ፥ ጳውሎስ ባህሪያት ማጥናት።

*<u>3. Deductive Bible Study:</u>*

- ከአጠቃላይ ሃሳብ ወደ ዝርዝር ሃሳብ መሄድ ነው። አብዛኛው የቤተክርስቲያን ዶክትሪን፥ የስነ-መለኮት ትምህርት መፃህፍት የተዘጋጁት በዚህ መንገድ ነው።
- <u>ምሳሌ፥</u> እግዚአብሔር የማይለወጥ፥ የማይናወጥ የዘላለም አምላክ  ነው። (ሚል 3፡6)

*4. Inductive Bible Study:*

- ከዝርዝር ሃሳቦች ወደ አንድ አጠቃላይ እውነት መድረስ ነው፡፡ የተዘረዘሩትን እውነቶች በመመልከት አጠቃላይ ወደ ሆነ መደምደሚያ ለመድረስ የምንጠቀምበት መንገድ ነው፡፡ በመፅሐፍ ቅዱስም ውስጥ በአንዳንድ ክፍሎች ተጠቅሷል፥ ***ለግል፥ ለቡድን ወይንም ለመፅሐፍ ቅዱስ ትንታኔ ይጠቅማል፡፡

- Inductive: መስተጋብዓዊ
- Logic: ሥነ-አመክንዮ
- ስለዚህ የአማርኛ ትርጉሙ፥ "መስተጋብዓዊ ሥነ-አመክንዮ" ማለት ነው፡፡

**ለምሳሌ**፥ ዘፍጥረት 3፥9-14 / ሉቃስ 9፥18-22 / ማቴ 16፥13-20 / ማር 8፥14-21

**ፘ. ይህ አጠናን ሦስት ደረጃዎች አሉት፥**

*1. መመልከት፥ (Observation)*

- በምናጠናው ክፍል ውስጥ ያሉትን በግልጥም ሆነ በስውር (By Implication) የተገለጡትን ሀቆች፥ ሃሳቦች፥ ድርጊቶች ለቅሞ ማውጣት ነው፡፡

- በመመልከት ጊዜ መጠየቅ ያለብን ጥያቄ የሚከተለው ነው፥
"ይህ ክፍል ምን ይላል?"

*ምሳሌ፥ የሐዋርያት ሥራ 17፥11*

*2. መተርጎም፥ (Interpretation)*

- የሃቆቹን ትርጉም (ፍቺ) መወሰን፥ መግለጥ፥ ማጉላትና ማዕከላዊ መልዕክቱን መረዳት ማለት ነው፡፡

- በመተርጎም ጊዜ ልንጠይቀው የሚገባን ጥያቄ የሚከተለው ነው፥
"ፀሃፊው ምን ለማለት ነው የፈለገው?"

*ምሳሌ፥ 2ጢሞ 2፥7*

*3. ማዛመድ፥ (Application) እኔታ*

- ለተለገለጠውና ለተማርነው እውነት ራስን መክፈት ነው፡፡
  የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት የመጨረሻ ዓላማውና ግቡ ይኼው ነው፡፡
- "ይህ ለኔ ምን ማለት ነው?"
- ከዚህ ክፍል ለግሌ የምማረው ምንድነው?
- በህብረትስ ልንማረው የሚገባን ምንድን ነው?

*<u>ምሳሌ</u>፥ ሉቃስ 10፥28*

**ተመልከት** Look → **አስብ** Think → **አያይዝ** Link

**<u>ልምምድ</u>፥ ማር 7፥31-37 እና ማር 8፥22-28 ያሉትን ታሪኮች ካነበብክ በኋላ፥ የሚመሳሰሉበትንና የሚለያዩበትን ነገሮች ዘርዝር፡**

***<u>በመመልከት ጊዜ የሚከተሉትን ማወቅ አስፈላጊ ነው፥</u>***

<u>፩. የፅሁፉን (የመፅሐፉን) አይነት መወሰን፥</u>

- በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን መፃህፍት አንድ አይነት እንዲሆኑ አድርገን በአንድ አይነት መልክ ልናጠናቸው አንችልም፡፡ መፅሐፍ ቅዱስ ትልቅ ቤተ መፃህፍት ነው፡፡ ስለዚህ በመጀመሪያው ደረጃ

“በመመልከት” ጊዜ አስቀድመን ፅሁፉ ምን አይነት እንደሆነ መወሰን አለብን።

*መፅሐፍ ቅዱስ በአራት ሊከፈል ይችላል፥*

*1. የታሪክ/የድርጊት/ምንባብ (Narrative Passages)*

- የመጀመሪያዎቹ የብሉይ ኪዳን 17 መፃህፍት፥ የመጀመሪያዎቹ የአዲስ ኪዳን 5 መፃህፍት። እነኚህ መፃህፍት ሰዎችን፥ድርጊቶችን፥ የሰዎችን ምልልስ ይተርካሉ።

- ዋና ትኩረታቸው ድርጊት ላይ ነው። (Describe)

*2. የንግግር/የመልዕክት/ምንባብ፥ (Discourse Passages)*

- የነቢያት ትምህርቶች፥ የአዲስ ኪዳን ስብከቶች (የጌታም ሆነ የደቀመዛሙርት)። ለምሳሌ፥ ማቴ 5-7፤ የሐዋ ሥራ 2፡16-36)፥ ሐዋርያት የፃፉአቸውን ደብዳቤዎች። (ለምሳሌ፥ የጴጥሮስ፥ የዮሐንስ፥ የጳውሎስ፥ የያዕቆብ መልዕክቶች፥ ዘዳግም) እነኚህ ፅሁፎች ፀሃፊው/ተናጋሪው/ሰሚዎቹ እንዲለውጡት የፈለገው እምነት/ባህሪ ላይ ነው ትኩረታቸው።

- ዋና ትኩረታቸው ፀሃፊው/ተናጋሪው/ሊያስተላልፈው በፈለገው ልመና/ሃሳብ ላይ ነው። (PERSUADE)

*3. የግጥም/የጥበብ ምንባብ (Poetry/Wisdom Literature)*

- ኢዮብ፥ መዝሙረ ዳዊት፥ ምሳሌ

- እነዚህ መፃህፍት የመፅሐፍ ቅዱስን 1/3 ቦታ ይዘዋል።

- ዋና ትኩረታቸው የሰውዬው ውስጣዊ ስሜት (Intuition) ጭልታ ላይ ነው።

*4. የትንቢት ምንባብ፥ (Apocalyptic)*

- ዳንኤልና ራዕይ በህልም በራዕይና በተምሳሊት የእግዚአብሔርን ዕቅድ በታሪክ ውስጥ ይገልጣሉ።
- ማስገንዘቢያ፥ ነቢያት ይሰጡት የነበረው ትንቢት/ትምህርት/

ከሁሉም አይነት የተውጣጣ ነው::

- ዋና ትኩረታቸው እግዚአብሔር ለህዝቡ ያለው ሐሳብና ዓላማ ላይ ነው::

## <u>ልምምድ፥</u> የፅሁፉን አይነት መወሰን::

- ÷ መዝ 73 ÷ ዳንኤል 7 ÷ ዘዳግም ÷ የ

## <u>፬. ሐቆችን ማግኛ ጥታዌዎችን መጠየቅ፥ (Fact Finding Questions)</u>

### <u>*1. ማን? የት? መቼ? (Who? Where? When?)*</u>

- የድርጊቱን/የመልዕክት ሁኔታ (Setting) ያመለክተናል::

### <u>*2. ምን? እንዴት? ለምን? (What? How? Why?)*</u>

- ቀናውን ድርጊት/መልዕክት አጥርተን እንድናይ ይረዱናል::

### <u>*3. ስለዚህ? (So what was the result?)*</u>

- የድርጉቱን ውጤት/ጣሪያ (Climax) ያመለክተናል::

<u>**ምን?**</u>

- በተራኪ ምንባብ፥ ዋናው ድርጊት (Event/Action)
- በንግግር/በመልዕክት/ምንባብ፥ ዋና ሃሳብ (Argument)
- በግጥም ምንባብ፥ የፀሐፊው ምስክርነት/ውስጣዊ ስሜት (Intuition)
- በትንቢት ምንባብ፥ የነቢዩን ራዕይ ያመለክታል (God’s Divine Purpose)

ማን?
የት?
መቼ?

ምን?
እንዴት?
ለምን?

ስለዚህ?

# <u>ልምምድ፥</u> ማርቆስ 3፥1-6

<u>ማን?</u>

- ኢየሱስ፥ እጁ ሽባ የሆነው ሰው፥ ፈሪሳውያን፥ የሄሮድስ ወገን (ሌሎች?) …. ደቀ መዛሙርት፥ በምኩራብ ያለው ህዝብ

<u>የት?</u>

- በምኩራብ፥ (በቅፍርናሆም? 2፡1)

<u>መቼ?</u>

- በሰንበት፥ (ለአገልግሎቱ መጀመሪያ አካባቢ?)

<u>ምን?</u>

- ኢየሱስ ሰውዬውን ፈወሰ።
- ፈሪሳውያን ከኢየሱስ ጋር ተጋጩ።

<u>እንዴት?</u>

| | |
|---|---|
| አዘዘው፥ ሰውዬውም ታዘዘ ኢየሱስ ነው ጅማሬውን (Initiative) የወሰደው። | ጥያቄ ይጠይቃቸዋል ከዚያ ሰውዬውን ይፈውሳል። ይህንን በድፍረት ነው ያደረገው። |

<u>ለምን?</u>

| | |
|---|---|
| በሰንሰለት መልካም ማድረግ ትክክል ነው፥ ህይወትን ማዳን:: | መልካም ለማድረግም ሰዎችን ሙሉ (Whole) እንዲሆኑ ነው የመጣው:: |

**ስለዚህ?**

- ፈሪሳውያን ከሄሮድስ ወገን ጋር ተማከሩበት::

## ***ልምምድ፥*** ማርቆስ 4፥35-41

**ምዕራፍ ሶስት**

***መመልከት፥***

- የፀሐፊው የመልዕክት ዕድገት ለማግኘት ዝርዝር ሃሳቦችን ማየት::

**፩. ሃሳቡን (Persuasion) ለማቅረብ የተጠቀመውን መንገድ ተመልከት፥**

| | |
|---|---|
| • ምክር<br>• ማፅናናት<br>• ትዕዛዝ | • ማስጠንቀቂያ<br>• ተስፋ<br>• ጥያቄ |

## ***ልምምድ፥*** 1ጴጥሮስ 4፥12-19

## ፬. የደራሲውን/የፀሐፊውን/ትኩረት ተመልከት፥

1. የቃላት፥ የሃሳብ ወይንም የሰዎች መደጋገም የግድ የፀሀፊውን ትኩረት ባያሳይም፥ አብዛኛውን ጊዜ ግን ሊያሳይ ይችላል፡፡ ( Repetition)
2. ፀሐፊው በማመሳሰል ትኩረቱን ሊያሳይ ይችላል፡፡ (Comparison)
3. በማነፃፀርም ትኩረቱን ሊያሳይ ይችላል፡፡ ማነፃፀር ከማመሳሰል ይልቅ ሐሳቡን በተለያዩ አቅጣጫዎች እንድናየው ይረዳናል፡፡
4. ለሃሳቡ የተሰጠው የቦታ ስፋትም ትኩረቱን ያሳያል፡፡

## ፫. የፀሐፊው የሀሳብ አደራደር/ቢጋር (Pattern)

1. ሳቢያና ውጤት (Cause and Effect)

2. መንገድ ለግብ (Means to an End)

    - አንድን እውነት ለማስጨበጥ ሆነ ተብሎ የሚተነተን ሃሳብ/ ድርጊት፡፡

    ምሳሌ፥ ጌታ ኢየሱስ የሰጣቸው የነበረው ምሳሌያዊ አነጋገሮች ዓላማ ነበረው፡፡

3. የሃሳብ ዕድገት (Progression of Thought)

4. ኃይለ-ቃል (General Statements)

    ምሳሌ፥ መዝሙረ ዳዊት

**ልምምድ፥ ሉቃስ 15፥1-32**

## ምዕራፍ አራት

### መመልከት፥

፩. ፀሐፊው የተጠቀመባቸውን አያያዥ ቃላት መመልከት፥

- የሃሳቡን አቅጣጫ፥ የሃሳብ ለውጥ ካለ ያመለክቱናል፡፡

ምሳሌ፥ ነገር ግን፥ ዳሩ ግን፥ ቢሆንም፥ እና ፥እንደዚህ ከሆነ ፥ ስለዚህ
ምክንያት፥ ስለዚህ፥ ወይም፥ እንደ ፥ ወዘተ …

**ልምምድ፥** 1ጴጥሮስ 4፥12-19

፪. የ

- "ምናብ፥ አንድን ነገር በሃሳብ ውስጥ ማየት ማለት ነው፡፡"

1. በተራኪ ምንባብ፥

- ሰዎችና ሁኔታዎችን በውስጥ ሀሳብህ፤ ልታያቸው፥ ልታዳምጣቸውና በስሜታቸው ልትገባ ሞክር፡፡

2. በመልዕክት ምንባብ፥

- ፀሐፊው የገለፀውን ሁኔታ ወይንም ችግር እዚያ እንዳለህ ሆነህ ልታየው ሞክር፡፡

*3. በግጥም ምንባብ፥*

- **ከፀሐፊው ስሜት ጋር ራስህን አመሳስል** (Identify)

*4. በትንቢት ምንባብ፥*

- **ነቢዩ የታየውን፤ ህልም፥ ራዕይም ሆነ ተምሳሊት ልታይ ሞክር፡፡**

**ልምምድ፥ በድራማው ውስጥ ግባ፥ ማር** 4፥35-4

*በክፍሉ ሃሳብ ላይ አተኩር!*

**፫. ጥያቄዎችን ከመጠየቅ ወደኋላ አትበል፡፡**

- **ጠይቀህ ወዲያው በመጣው ቀላል መልስ ብቻ አትርካ፡፡ ጠይቅ፥ ጠይቅ፥ ጠይቅ**!!!

*1. ለማወቅ የምትጓጓ ሁን፡፡*

- **ህቆችን እንዲሁ** (for granted) **አትውሰዳቸው፡፡**

*2. ከፀሀፊው ጋር ልትጫወት ሞክር፡፡ (Interact with the Writer)*

*3. ሰዎቹ ያሉበትን ሁኔታ ለማየት ሞክር፡፡*

- **የሰዎቹ የስሜት ደረጃ ምን ይመስላል**? **ምላሽ አሰጣጣቸው እንዴት ነው**? **ስለሰው ፍጥረት ምንን ታያለህ**?

*4. በሰዎቹ ውስጥም ገብተህ ለማየት ሞክር።*

- **ዝንባሌያቸውን** (Attituded) **የድርጊታቸውን አቅጣጫ** (Intentions) ፥ **መንስኤ** (Motives) **የሰዎቹ መልካም ነገር።** (Potential/Gifts)

*5. በእምነት ማደጋቸውንም እይ።*

- **ስላላቸው ተስፋ፥ ጥማት፥ ትግል፥ የማስተዋል ዕድገት፥ እውነትን ላለመልቀቅ ያላቸው ጥረት፥ ያለማመናቸው ዕድገት ተመልከት።**

**ልምምድ፥ ማርቆስ** 4፥35-41

**ምዕራፍ**

***መተርጎም፥***

**፮. የፀሐፊውን ዋና ዓላማ ወስን፥**

- **በክፍሉ ውስጥ የተገለፁትን ሀቆችና ሃሳቦችን የሚያያይዝ አንድ ጭብጥ ሃሳብ/መሪ ሃሳብ** (Theme) **ልታይ ሞክር።**
- **ቁልፍ ቃላትን፥ ሃረጎችን፥ ዓረፍተ ነገሮችን ማስተንተን፥**
- **በመተርጎም ጊዜ የሚረዱ መመሪያዎች፥**

*1. ቀጥተኛ ትርጉም (Natural Meaning) ፥*

- **የተለየ ትርጉም ከሌለው በስተቀር ቃላቶችን እንዳሉ በጥሬያቸው** (Literally) **መውሰድ።**

***ምሳሌ፥ ፀጋ፥ ኃጢያት፥ እምነት፥ ወዘተ....***

*2. ዕንስ ትርጉም/ነባር ትርጉም (Original Meaning) ፥*

- በጊዜው ለነበሩት ለተፃፈላቸው ሰዎች የነበረውን ትርጉም ማየት በጣም አስፈላጊ ነው::

***ምሳሌ*÷ *ለምፅ*÷ *ማር*** 1÷40-45

*3. ተባባሪ ትርጉም (Consistent Meaning)÷*

- ከክፍሉ አውደ ምንባብ ጋርና ከሌሎች የመፅሐር ቅዱስ ክፍሎች ጋር የሚስማማ ትርጉም መስጠት::
- የምንፈልገውን ሃሳብ እንዲልልን አናስገድደው::

***ምሳሌ*÷ *ማቴ*** 15÷ 21-28

## ፪. የተቻለንን ያህል መረዳት ከሞከርን በኋላ÷

- ለማናውቀው ሃሳብ ብቻ ፍቺውን ለማወቅ የሚረዱ መፃህፍትን መጠቀም:: የመፃህፍቶቹን ድምዳሜ እንደራሳችን ጥረት አድርገን ልንወስደው አይገባም::

- ኮሜንታሪ÷ መዝገበ ቃላት÷ ኮንኮርዳንስ÷ አትላስ÷ ወዘተ...

## ፫. ሀቆችን መመዘን÷

- “አስፈላጊው ሃሳብ የትኛው ነው?” ብሎ መጠየቅና ጎላ ብሎ የሚታየውን ለማየት መቻል በጣም አስፈላጊ ነው::

***ምሳሌ*÷ *ማር*** 3÷1-6

- የሰውየው መፈወስ ከድርጊቶቹ አንዱ ቢሆንም÷ የፀሀፊው ትኩረት ግን በፈሪሳውያን ክስ ላይ እንደሆነ ከዕውደ ምንባቡ ልናይ እንችላለን:: (ማር 2÷23-28)

## ፬. ሃሳቦቹን ማያያዝ፦

- ሃሳቦቹ እንደተነባጠሉ አንተዋቸው፤ እናያይዛቸው።

**ምሳሌ፦** ዮሐ 8፥1-11

- “በድንጋይ ይውገራት” - ህግ አክባሪ
- “እኔም አልፈርድብሽም” - አፍቃሪ
- “ደግመሽ ኃጢያት አትስሪ” - ኃጢያትን የሚጠላ
- ስለዚህ “ኢየሱስ ኃጢያተኛን የሚወድ፤ ኃጢያትን ግን የሚጠላ ነው።” ልንል እንችላለን።

## ፭. የፀሐፊውን ዋና መልዕክት መጠቅለል፦ (Summary)

- ይህም ማለት ታሪኩን መድገም አይደለም። ዋናውን ማዕከላዊ ድርጊት/መልዕክት ይዘን ማጠንጠን ነው።
- “ማን? ምን ያደርጋል? በምን አይነት ሁኔታ? ከዚህ የተነሳ ምን ውጤት አስከተለ?”

# ምዕራፍ ስድስት

## መተርጎም፦

## ፩. ምንባቡንና (Text) ስለምንባቡ የተነገሩትን መለየት፦

1. **የምንባቡ ሀቅ** (Textual Fact)፦
   - መፅሐፍ ቅዱስ በቀጥታ በክፍሉ ውስጥ ያሰፈረው ሃሳብ።

2. **አንድምታ** (Implication)
   - በውስጠ ታዋቂ የተደበቀ ሀቅ (Expected Fact)።

3. **ጠቅላላ እውቀት** (General Knowledge)
- **ከሌሎች ምንጮች የተዘገበ/የተገኘ እውቀት፡፡**

4. **መተርጎም** (Interpretation)
- **በምንባቡ ሀቆችና ድብቅ ሀቆች ለማለት የተፈለገው ነገር፡፡**

5. **አስተያየት** (Opinion)
- **እንደ አንድ አማራጭ የተሰነዘረ ሃሳብ/አስተያየት ፣ ማስረጃ የሌለው ግን እንደ አማራጭ ሊወሰድ የሚችል፡፡**

6. **እኔታ** (Application)

7. **ምናብ** (Imagination)
- **አንድን ነገር በሃሳብ ውስጥ ማየት ማለት ነው፡፡**

8. **ግምት** (Speculation)
- **በጥቂት ወይም ያለምንም መረጃ የተሰጠ ግምት፡፡**

9. **መንፈሳዊ ማድረግ** (Spiritualization)
- **ከደረቅ እውነት ወደማይመስል የምሳሌታዊነት መለወጥ፡፡**

10. **ራስን ማመሳሰል** (Identification)
- **ሰዎቹ ባሉበት ሁኔታ ራስን ማስቀመጥ/ማየት፡፡**

## **ልምምድ፥ ማር** 4፥35-41

1. **ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ከረዥም የማስተማር ቀንና በግልም ለደቀ መዛሙርቱ ስለ ትምህርቱ ትርጉም ከመስጠት የተነሳ ደክሚቸው ነበር፡፡**

2. ኢየሱስ ከከባድ ስራ በኋላ ማረፍ እንደሚያስፈልግ ያውቅ ነበር፡፡

3. ከኢየሱስም ከስራችን መቼ ማረፍ እንደሚገባን መማር እንችላለን፡፡

4. በቁጥር 36 ላይ የተጠቀሱት ሌሎች ታንኳዎች በህይወት ባህር ላይ ከኢየሱስ ጋር ስንጓዝ ወደ ኋላ ልንተዋቸው የሚገቡን አለማዊ አስተሳሰቦች ናቸው፡፡

5. ከሚከቡት ተራራዎች የተነሳ የገሊላ ሀይቅ የተለማመዱት አሣ አጥማጆች እንኳን ሊቆጣጠሩት የማይችሉት ድንገተኛና ኃይለኛ ሞገድ ያስነሳል፡፡

6. ፀሐይዋ ከነሱ በስተኋላ እየጠለቀች ነበር፡፡ የጨለሙ ደመናዎች ሊከቧቸው ጀመሩ፡፡ ከዚያም ሞገድ የተሞላ ነፋስና ውሃ አጥለቀለቃቸው፡፡

7. ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ይልቅ በጣም ስለሰራና ስለደከመ ነበር የተኛው፡፡

8. ኢየሱስ በእውነቱ የተኛ ያስመስላል እንጂ አልተኛም ነበር፡፡ አንድ አይኑን ገርበብ አድርጎ ማዕበሉ በረድ እስኪል ይጠብቅ ነበር፡፡ ከዚያምተነስቶ ፀጥበል ይለዋል፡፡

9. በቁጥር 38 ላይ ያለው ጌታ የተንተራሰው ትራስ የእግዚአብሔርን ፍቅር ያሳያል፡፡

10. ደቀመዘሙርቱ በጌታ ተቆጥተው ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ራሱ እንሻገር ብሎ አሁን ግን ቸል ያለ ስለሚመስል፡፡

11. ችግር የሌለብን ከማስመሰል ይልቅ የቁጣ ስሜታችንም እንኳ ቢሆን ብንገልፀው ኢየሱስ ይወዳል፡፡

12. እኔም ብሆን በእንዲህ አይነት ጊዜ በኢየሱስ ላይ እቆጣ ነበር፡፡

13. ደቀ መዛሙርቱ በስሜት በኩል ያሳዩት ሽግግር ከፍርሃት ወደ ቁጣ፥ ከዚያም ወደ አድናቆት ነው፡፡

14. ከዚህ ሁኔታ (Event) በፊት ደቀ መዘሙርቱ ጌታ ኢየሱስን እንደ ታላቅ አስተማሪና ፈዋሽ ይቆጥሩት ነበር፥ እንጂ፤ እንደ ፈጣሪና ጌታ አላመኑበትም፡፡

15. ይህ ተዓምራት ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ያሳያል፡፡

16. ችግር ሲደርስብን እንርበተበታለን እንጂ፥ ለእግዚአብሔር ግን ምንም የሚያስደነግጥ አይደለም፡፡ አሁንም ቢሆን እግዚአብሔር ፍርሀታችንንም ሆነ ችግራችንን ሊቆጣጠረው ይችላል፡፡

17. ኢየሱስ ፀጥ ያደረገው ማዕበሉን ብቻ ሳይሆን፥ የደቀ መዛሙርቱንም ፍረሃትና በልባቸው ውስጥ የነበረውን ንውጥውጥታም ጭምር ነው፡፡

***መልስ፥***

1. **አንድምታ/አስተያየት** (Implication/Opinion)
2. **አስተያየት** (Opinion)
3. **እኔታ/ግምት** (Application)
4. **መንፈሳዊ ማድረግ** (Spiritualizing)
5. **ጠቅላላ ዕውቀት** (General Knowledge)
6. **ምናብ** (Imagination)
7. **አስተያየት/አንድምታ** (Opinion/Implication)
8. **ግምት** (Speculation)
9. **መንፈሳዊ ማድረግ** (Spiritualization)
10. **አንድምታ** (Implication)
11. **እኔታ** (Application)
12. **ራስን ማመሳሰል** (Identification)
13. **መተርጎም** (Interpretation)
14. **አስተያየት** (Opinion)
15. **እኔታ** (Application)

16. አንድምታ (Implication)

***<u>ምዕራፍ ሰባት</u>***

***<u>ማዛመድ፥</u>***

***የተረዳነውን መረዳት እንዴት በስራ ላይ እናውለዋለን?***

***<u>፩. መፅሀፍ ቅዱስን ወደ ህይወትህ አምጣው፥</u>***

- እዚህ ከተጠቀሱት ሰዎች ጋር እንዴት እንመሳሰላለን?
- የነሱ ችግር ከኛ ችግር ጋር እንዴት ይመሳሰላል?
- በነሱ ሁኔታ ብንቀመጥ የእግዚአብሔር ምክር ምን ያህል እኛንም ይመለከታል?
- የሰዎቹ ምላሽ (አዎንታ/አሉታ) እኛ ካለንበት ሁኔታ ምን ያህል ይሄዳል?

1. የተረዳኸውን አሁን ካለው የኑሮ ሁኔታ ጋር አያይዘው፥
2. ነገር ግን አስተውል!

- አስቀድመህ በሚገባ የክፍሉን ሀሳብ ካልተመለከትከውና ካልተረጎምከው፣ ከህይወትህ ጋር የምታዛምደው ነገር ወይ ያልበሰለ ይሆናል፣ ወይንም ደግሞ ከላይ ከላይ የሆነ ጥልቀት የሌለው ይሆናል:: ከህይወት ጋር የማይገናኙ በጣም አጠቃላይና ምንም ትርጉም የሌላቸውን ማዛመዶች አስወግድ::

***ምሳሌ፥*** "የበለጠ ዕምነት ሊኖረን ይገባል::"

"ለሁሉም ሰው መመስከር አለብን::"

- ይልቁንም የበለጠ ግላዊ፥ ግልጥና በአንድ ነገር ላይ ያተኮረ (Specific) የሆኑ ነገሮችን የምታካፍል ሁን::

## ፪. ህይወትህን በመፅሀፍ ቅዱስ ፊት አምጣው::

- የተማርከው ትምህርት (ክፍል) ለግልህ፥ ለህብረትና በአጠቃላይም ለእግዚአብሔር ህዝብ ምን ማለት እንደሆነ ልታይ ሞክር:: በእግዚአብሔር እውነት ሲመዘን ህይወትህ ምን ያህል ይመዝናል? ህይወትን መለወጥ የሚችል የእግዚአብሔርን ሀሳብ ምን ታያለህ?

- *በዚህ ክፍል ውስጥ የምታየው የሰው ባህሪ ምን ያህል ህይወት ሊያስለውጥ ይችላል?*

- ልብህን የሚነካ ምሳሌ ታያለህን? ማስጠንቀቂያስ?
- ንስሃ ልትገባበት የሚገባህ ኃጢያት?
- የታደሰ ተስፋ? የተጠናከረ እምነት?
- ልትወስዳቸው የሚገቡህ እርምጃዎች?

- ማዛመድ ህይወትህንና የኑሮህን አቅጣጫ እስካላስለወጠህ ድረስ ንድፈ-ሐሳብ (Theory) ብቻ ሆኖ ነው የሚቀረው:: ስለዚህ እግዚአብሔር የገለጠልህን እውነት በህይወትህ እንድትተረጉመው ለጌታ ፀጋ ትጋ!! እግዚአብሔር ስለተናገረህና ቃሉንም ስለገለጠልህአመስግነው ፥ ... እንዲረዳህም በፀሎት በፊቱ ልብህን አፍስስ::

**ልምምድ**፥ **ማር** 4፥ 35-41

- ለግ... Corporate) ... ድ እርምጃዎችን አውጣ::

**ልምምድ**፥ **ሉቃስ** 5፥1-11

*ዕው...*

- ... ዳጅነትን አትርፏል:: ጴጥሮስንም እንዲሁ በ

## ፩. መመልከት፥

*ማን?*

- ኢየሱስ፥ ተወዳጁ ሰባኪና መምህር::
- ህዝቡ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት የጓጓ::
- አሳ አጥማጆች፥ ሌሊቱን በሙሉ ሲያጠምዱ አድረው ምንም ስላላገኙ የተዳከሙና ተስፋም የቆረጡ፤ ከዚህ የተነሳ በአካባቢያቸው ያለውን የሚሆነውን ለማወቅ ስሜት የማያስጣቸው::
- ስምዖን ጴጥሮስ፥ ኢየሱስ ትኩረት (Attention) የሰጠው::
- አንድምታ፥ ኢየሱስ ትኩረቱን ከህዝብ፥ ወደ ጥቂቶቹ ከዚያም ወደ ግለሰብ አዙሯል::

*የት?*

- በጌንሳሬጥ ባህር (ቁ.1) - ኢየሱስ የትውልድ ቦታ (አውራጃ) የሚገኝ የገሊላ ቦታ::
- *አንድምታ፥* ኢየሱስ ወደ ስራ ቦታቸው ነው የመጣው::

*መቼ?*

- በማለዳ ከብዙ ድካምና ውድቀት በኋላ (ቁ. 4)::
- አንድምታ፥ ስሜታቸው በቀዘቀዘበት ጊዜ ነው የመጣው::

*ምን?*

- ኢየሱስ ስመዖንንና ጓደኞቹን አብረውት እንዲያገለግሉ ጠራቸው::
- *አንድምታ፥* ከዐውደ - ምንባቡ፥
- ኢየሱስም ሆነ እነ ስምዖን እርስ በእርሳቸው ለመጠናናት በቂ ጊዜ (አንድ ዓመት ያህል) ነበራቸው::

*እንዴት?*

*የኢየሱስ አጠራር እድገት ነበረው፥*

1. ሁኔታቸውን በመመልከት (ቁ. 1-2)
2. ጴጥሮስን ወደ ህዝብ አገልግሎቱ በማቅረብ (ቁ. 3)
3. ታላቅ ባለ ፈተና (Challenge) በመፈተን (ቁ. 4)
4. ቀጥተኛ የሆነ ኃላፊነት እንዲወስድ በማድረግ (ቁ. 5-7)

5. ስለራሱም ሆነ ስለ ኢየሱስ የነበረው አመለካከት ትክክል አለመሆኑን ለማሳየት (ቁ. 8-9)

6. ልቡን በማፅናናትና ጥሪውን በመግለፅ (ቁ. 10)

*ለምን?*

- ኢየሱስ ሠራተኞች ያስፈልጉት ነበር፡፡ የህዝቡ ጥማት ሰራተኞችን እንዲመርጥ አስገድዶት ነበር፡፡
- ኢየሱስ ብቻውን የሚሰራው መስሎ አልታየውም፡፡
- አንድምታ፥

*ስለዚህ?*

- አሳ አጥማጆቹ ሁሉን ትተው ተከተሉት፡፡

- *አንድምታ፥* ኢየሱስ ታላቅ አስተማሪ ብቻ ሳይሆን በነሱም ስራ ላይ ጌታ መሆኑን በአይናቸው በተመለከተ ጊዜ ነው ሊከተሉት የቻሉት፡፡

፪. መተርጎም፥

- ኢየሱስ እነኚህን አሳ አጥማጆች ከአሁን በፊት ቢያገኛቸውም፥ አገልግሎቱ እያደገ ሲሄድ ሰውን የሚያጠምዱ እንዲሆኑ የሚጠራቸው አሁን ነው፡፡ ከአሳ አጥማጅነት ወደ ሰው አጥማጅነት፤ ትልቅ ሽግግር የከበረም ጥሪ ነው፡፡ አቀራረቡም በስራ የተገለፀና ደረጃ በደረጃም ስለነበረ በንግግር ከረታቸው ይልቅ በድርጊቱ ነው ልባቸውን የማረከው፡፡ አሳም በማጥመድም እንኳን ሳይቀር ከነሱ የበለጠ ዕውቀት ያለው መሆኑን ሲያውቁና ዳግም በአገልግሎቱም ሲጋብዛቸው ጌትነቱንእየተረዱ ሄዱ፡፡

፫. ማዛመድ፥

- በማዛመድ ጊዜ የተለያየ ገፅታ ሊኖረን ይችላል፡፡

- ለግል ወይንም ለህብረት የሚሆነን ማድረግ እንችላለን፡፡

*1. ደቀ መዛሙርትን እንዴት ልናፈራ እንችላለን?*

- የመጀመሪያዎቹ ልንወስዳቸው የሚገቡን እርምጃዎች ምን ምን ናቸው?
- ለጌትነቱ ምን አይነት ዝንባሌ ሊኖረን ይገባል?
- ደቀ መዛሙርት የሚሆኑትን እንዴት እናውቃቸዋለን?
- ሌሎችን ደቀ መዘሙርት የሚያፈሩ እንዲሆኑ እንዴት እናደርጋቸዋለን?

*2. እምነትና መታዘዝ፥*

- ኢየሱስን ያለመታዘዝ ልናምነው እንችላለን?
- ምን ያህል ማወቅ አለብን ከመታዘዛችን በፊት?
- ከመታዘዛችን በፊት፥ የማያስፈልጉ ግን የምናደርጋቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው?
- አለመታዘዛችን ምን ጠንቅ ያመጣል? ምንስ እናገኛለን?

*3. እምነትና የሚታዩ ምልክቶች፥*

- የሚታዩ ነገሮች ለእምነት ምን ያህል አስፈላጊ ናቸው?
- ምን አይነት ሰዎች ናቸው ምልክቶች የሚያስፍልጓቸው?
- የአሁኑ ዘመን የእግዚአብሔር ምልክቶችና የኃይሉ መግለጫዎች ምንድን ናቸው?
- በኢየሱስ ጌትነት እንድታምን የሚረዳህ ምንድነው?

## ልምምድ፥ ፊሊሞና

**ምዕራፍ ስምንት**

**የቡድን የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት፥**

<u>፩. አስፈላጊነቱ፥</u>

1. የተካፋዮቹን አእምሮ ሙሉ በሙሉ እንዲጠቀሙበት ስለሚረዳ ፍላጎታቸውን ያዳብራል (የሐዋ. ሥራ 17፥11)
2. ከተሳሳተ ግላዊ እምነትና አመለካከትም ለመጠበቅ (የሐዋ. ሥራ 18፥26)
3. በሰባኪ ከሚሰሙት ይልቅ፥ በግላቸው የቃሉን ምስጢር እንዲያገኙት ስለሚረዳቸው ደስታቸውን ይጨምራል።
4. ለምንባቡም ፍትህ (Justice) ያደርጋል። የመጨረሻ ወሳኝ ባለስልጣን በዚያ ክፍል ውስጥ ያለው ቃል ስለሆነ አትኩረን እንድናጠናው ይረዳናል።
5. በጣም በሰለጠኑ የሥነ-መለኮት ሊቃውንት የተመሰረተ ስለአይደለ ሁሉም እንዲካፈሉ ያበረታታቸዋል። መሪው ወሳኝ ባለስልጣን እንደሆነራሱን ሊያይ አይገባውም እርሱም ራሱ ተማሪ ነው። የተማሪነት መንፈስ ሊኖረው ይገባል።
6. አንዱ ከሌላው በሚያገኘው የቃሉ መገለጥ እንዲታነፅ ለመንፈስ ቅዱስ ትልቅ ስፍራን ይሰጣል።
7. ብስለት ያላቸው መሪዎችን ላማፍራት ይረዳል።
8. ሃሳቡን ለመግለፅ ያደፋፍራል፥ ለመተዋወቅም ለመሸካከምም ይረዳል። (1ተሰ. 2፥8) (ቆላ. 3፥16)
9. እግዚአብሔር በቃሉ በሰዎች ህይወት ውስጥ የሚያመጣውንም ለውጥ ለማየት ይረዳል። (1ተሰ. 1፥6-8)
10. ከማያምኑ ሰዎችም ጋር ለማጥናት ይረዳል።

<u>፪. የመሪ ዝግጅት፥</u>

1. የመሪ ዋናው አላማ ሰዎችን ከቃሉ ጋር ማገናኘት ነው።
2. ከመዘጋጀቱ በፊት ስለራሱና ስለቡድኑ እግዚአብሔር ቃሉን እንዲገልጥበቅንነት መፀለይ አለበት።
3. ከእግዚአብሔር ጋር መስራት ትልቅ ዕድል እንደሆነ መረዳትና ማመስገን፥ አገልግሎቱንም ማክበር።

4. በቡድኑ ሁኔታ ሳይወሰን እግዚአብሔር ሊናገር እንደሚችል ማመን አለበት::

5. የክፍሉን ሃሳብ በመጀመሪያ ለራሱ ማጥናት÷ ከዚያም ቡድኑን እያሰበ ደጋግሞ ማጥናት::

## ፫. በጥናት ጊዜ የመሪው ድርሻ÷

1. የተፍታታ ሁኔታ እንዲኖር አበረታታ:: በችግር መዋጥ÷ አይነ- አፋርነት÷ ያለመብቃት ስሜት÷ ራስን ለመደበቅ መሞከር ለጥናቱ እንቅፋት ሊሆኑ ይችላሉ:: በፍቅር ከቀረብካቸው ግን ልባቸውን መክፈት ይጀምራሉ::

2. ራስህን ለመሆን ሞክር:: አንተም ፈታ በል:: - BE NATURAL!

3. በተቻለ መጠን ሁሉም ሊተያዩ እንደሚችሉ ክብነት ይኑረው::

4. የቡድኑን አባላት በቅርበት ልታውቃቸው ሞክር:: ምን እንደሚ ያስፈራቸው÷ እንደሚያሳስባቸው÷ የቤተሰባቸው ሁኔታ÷ የመጡበትም የአስተዳደግ ሁኔታ ሳይቀር ልታውቅ ሞክር::

5. ሰዎችን ልታጳምጣቸው የምትችልበት ትዕግስት ይኑርህ:: ያሉትን ብቻ ሳይሆን ለማለት ያልፈለጉትንም÷ ለምን እንዳሉትም ልትረዳላቸው ሞክር::

6. ጥያቄዎችህን በጥበብ ተጠቀም:: ለልምምድ የሚመጣ ነገር ነው:: ቶሎ እንዲመልሱልህ አታስጨንቃቸው÷ ለማሰብ ጊዜ ስጣቸው:: አባላቱም እንዲጠይቁ አበረታታቸው፤ የተጠየቀውንም ጥያቄ መልሰህ ወደ ቡድኑ አቅርበው::

7. ሃሳባቸውን እንዲገልፁ ነፃነት ስጣቸው:: ነገር ግን በክፍሉ ሀሳብ እንዲወሰኑ እርዳቸው:: አከራካሪ የሆኑ ሀሳቦች ሲነሱ አትፍራ:: የቡድኑ ጤንነት ነው:: ሆኖም አስፈላጊ ባልሆኑ ነገሮች ላይ ጊዜ ብዙ እንዳይጠፋ ተቆጣጠር::

8. ድርቅ ያለ እውነት (Dogmatism) በተቻለህ መጠን ልታስወግድ ሞክር:: ያለህን እውነት በድርቅና ከምትናገረው ይልቅ÷ በረጋ መንፈስ ስታቀርበው በቡድኑ ተቀባይነት ይኖረዋል::

9. ስህተት በሆንክበት ነጥብ ላይ ስህተትህን ተቀበል:: አንተም ልትሳሳት እንደምትችል እወቅ::

10. በጣም አስፈላጊ ካለሆነ በስተቀር ከሌላ ቦታ የተለያዩ ጥቅሶችን ከማምጣት ተቆጠቡ::

## ፬. በውይይቱ መሀከል የሚነሱትን ችግሮች በጥበብ ለመፍታት ሞክር::

1. ዝምታን አትጥላ ወይ እያሰቡ ናቸው፥ ጊዜ ስጣቸው - ወይንም ጥያቄው አልገባቸውም፥ በሌላ መልክ ጠይቀው::

2. ስህተት መሆኑን ብታውቅ "ትክክል አይደለም" ብለህ አትመልስ:: በጥበብ ግን ልታርመው ሞክር::

3. አከራካሪ ነገር ሲነሳ ወደ ክፍሉ ሀሳብ ምራቸው::

4. አይነ አፋሮች ቀላል ጥያቄዎችን በመጠየቅ እንዲናገሩ አደፋፍራቸው::

5. ተናጋሪ የሆኑ ሰዎችንም ሌሎች እንዳይናገሩ ስለሚያደርጉ የሌላውን ስም በመጥራት ከመናገር እንዲቆጠቡ አድርጋቸው:: ቢያስፈልግ በግል አነጋግራቸው::

6. የተለያዩ ጥቅሶችንም በማምጣት ለመናገር የሚፈልጉትንም በክፍሉ ምንባብ የመወሰን አስፈላጊነትን አስረዳቸው::

## ፭. የቡድን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ካካሄድን በኋላ የቡድኑ አጠናን ሁኔታ ግምገማ ማካሄድ *(Evaluation)*

1. የቡድኑ ዓይነት፥
   - መሪ ብቻውን ተናጋሪ የሆነበት የጥናት ዓይነት፥



ችግሩ፥

2. የቡድኑ ዓይነት፥

- የቡድኑ አባላት የግል ውይይት የሚያካሂዱበት መሪው መምራት  ያቃተው ቡድን፥




ችግሩ፦

3. የቡድኑ ዓይነት፦

- አንድ የቡድኑ አባል ብቻ ተናጋሪ (ሰባኪ) የሆነበት ጥናት፦




ችግሩ፦

መፍትሄ፦

4. የቡድኑ ዓይነት፦

- መሪው ከእያንዳንዱ የቡድን ዓባላት ጋር ምልልስ የሚያበዛበት ጥናት፦




ችግሩ፥

መፍትሄ፥

5. የቡድኑ ዓይነት፥

- አንዱ የቡድኑ አባል ሳይታወቅ መሪ ለመሆን የሚሞክርበት ቡድን፥




ችግሩ፦

መፍትሄ፦

6. ሁሉም የቡድኑ አባላት የሚካፈሉበት መሪውም በሚገባና በመረዳት የሚመራበት፤ ሁሉም ከሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ሥር ሆኖ የሚማርበት ቡድን፡፡

- እያንዳንዱ የቡድን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እንዲህ ዓይነት ሊሆን ይገባል!


መሪ